የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| | | |
|---|---|---|
| አሥራ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፰<br>አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፱ | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 113[rd] Year No. 8<br>ADDIS ABABA 20[th] December, 2006 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፰/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፭፻፭

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፰/፲፱፻፺፱

## በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት የሚያስችል ስምምነት እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፳፫ ቀን ፪ሺ፫ በቱኒስ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፰/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

CONTENTS

Proclamation No. 508/2006

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Tunisia for the Avoidance of Double Taxation with Respect to Taxes on Income No. Ratification Proclamation.... Page 3505

## PROCLAMATION NO. 508/2006.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF TUNISIA FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME

**WHEREAS,** an Agreement for the Avoidance of Double Taxation with Respect to Taxes on Income (the Agreement) was signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Tunisia on 23[rd] January 2003, in Tunis;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia on its meeting held on 5[th] day of December, 2006 has ratified the Agreement;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Tunisia for the Avoidance of Double Taxation with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No.508/2006."

ያንዱ ዋጋ Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩ Negarit G. P.O.Box 80001

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቱኒዚያ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፳፫ ቀን ፪ሺ፫ በቱኒስ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት የሚያስችል ስምምነት ፀድቋል::

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል::

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**2. Ratification of the Convention**

The Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Tunisia, for the Avoidance of Double Taxation with Respect to Taxes on Income signed 23rd January 2003 is ratified.

**3. Power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to implement the Agreement in cooperation with the concerned Government organs.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come in to force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 20th day of December, 2006**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**